# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

## ጋዜጣዊ መግለጫ

**ብሔር ተኮር ማፈናቀልና እንግልት እንዲሁም**
**በልማት ስም በዜጎች ላይ የሚፈጸም ማፈናቀልና የንብረት ማውደም**
**በአስቸኳይ ይቁም!**

ኅዳር 16 ቀን 2008 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የምዝገባ ቁጥር 1146

www.hrco.org.et

## መግቢያ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ)፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) በኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር አንቀጽ 1(ሀ) እና በኢትዮጵያ ፍትሐ-ብሔር ሕግ ቁጥር ከ404-482 በተጻፉት ድንጋጌዎች መሠረት መስከረም 29 ቀን 1984 ዓ.ም. በአባላት የተመሠረተ የመጀመሪያው መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም ነው፡፡ ሰመጉ በበጎ አድራጎትና ማኅበራት ዐዋጅ ቁጥር 621/2001 መሠረት "ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ማኅበር" ሆኖ በምዝገባ ቁጥር 1146 በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ድርጅት ነው፡፡ ሰመጉ ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የሃይማኖት ተቋም፣ የብሔረሰብ ቡድን፣ ማኅበራዊ መደብ ወዘተ የማይወግን፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ነው፡፡ ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው፡፡ ሰመጉ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ እንዲሻሻል ላለፉት 24 ዓመታት የበኩሉን አስተዋጽዖ ሲያበረክት ቆይቷል፤ ዛሬም በባሰ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ቢሆን በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

ከበርካታ የመርሐ ግብር ተግባራቱ መካከል የሰመጉ መለያውና ግንባር ቀደም ተግባሩ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝ መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ማጣራትና በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው፡፡ ሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ መሄድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና እርማት እንዲደረግ ሲጮህና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁ ይቀጥላል፡፡ በ24 ዓመታት ቆይታው ሰመጉ 36 መደበኛ መግለጫዎችና 139 ልዩ መግለጫዎችን በተጨማሪም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል፡፡

ይህንኑ ልማድና መንፈስ በመጠበቅና በማሳደግም ሐሙስ ኅዳር 16 ቀን 2008 በኢትዮጵያ ሆቴል የጋዜጣዊ መግለጫ ጉባዔ (press conference) ተዘጋጅቷል፡፡ የጋዜጣዊ መግለጫ ጉባዔው ዓቢይ ዓላማ በአሳሳቢነታቸው ምክንያት የተመረጡ ሁለት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ጉዳይ ላይ መንግሥት ልዩና አስቸኳይ ትኩረት እንዲሰጥ መጠየቅ፣ መገፋፋትና ማብረታታት ነው፡፡ ጉዳዮቹ የሚመለከቷቸው ልዩ ልዩ አካላትም የዚህ ሐገራዊ ጥረት አካልና አጋር በመሆን፣ የመግለጫውን ሙሉና ትክክለኛ መንፈስ፣ ዓላማና ይዘት በማስተጋባትና ተዛማጅ ድጋፎችም በማድረግ፣ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ እንዲሻሻል በምናደርገው ጉዞና ጥረት ላይ ከጎናችን በመሰለፍ የሙያ፣ የዜግነትና የሞራል ግዴታቸውን እንዲወጡ በታላቅ ትሕትና እንጠይቃለን፡፡

# በዚህ ጋዜጣዊ መግለጫ የተካተቱት

## 1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ኖኖ አሎ ቀበሌ የተፈጸመ የመብት ጥሰት የመጀመሪያው ሲሆን፣ በዚህም የአንድ ሰው ሕይወት አልፏል፣ በ10 ሰዎች ላይ ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት ደርሷል 99 የሣር ክዳን ቤቶች በእሳት ተቃጥለው ወድመዋል፣ 25 የቆርቆሮ ክዳን መኖሪያ ቤቶች በእሳት ተቃጥለው ወድመዋል፤ በአጠቃላይ ከሠላሳ ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት ወድሟል፡፡ ሰመጉ ባለሙያዎችን በቦታው ድረስ በመላክ ይህን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት አጣርቶ «ብሔር ተኮር ማፈናቀልና እንግልት በአስቸኳይ ይቁም!» በሚል ርእስ ነሐሴ 2007 ዓ.ም 136ኛ ልዩ መግለጫ አውጥቷል፡፡ መግለጫውንም ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት እንዲደርሳቸው አድርጓል፡፡ ዳሩ ግን መግለጫው ከወጣ በኋላ የሰብዓዊ መብት ጥሰቱ እየተባባሰ ዜጎች በሰላም የመኖር መብታቸው እየተጣሰ ይገኛል፡፡



የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ Human Rights Council

መግለጫው ከወጣ በኋላ ነሐሴ 28 ቀን 2007 ዓ.ም ከሌሊቱ 6:30 አቶ አቢ ተክለ ማሪያም የቱባሴ በናኖ ወረዳ ናኖ ቁንደላ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑ አርሶ አደር [illegible] በያዙት መሣሪያቸው «ሮንድ» እንዲጠብቁ ታዝዘው እየጠበቁ ሳለ ተገድለዋል:: አስከሬናቸውም በ29/12/2007 ዓ.ም. አዲስ አበባ ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል ከተመረመረ በኋላ ነሐሴ 30 ቀን 2007 ዓ.ም ናኖ ቆንዳላ ቀበሌ ቆንዳላ ገብርኤል ቤተክርስቲያን የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል::



ሟች አቶ አቢ ተክለማሪያም
ዕድሜያቸው 50 እና የአስር ቤተሰብ አስተዳዳሪ ነበሩ።።

ከዚህ በተጨማሪ፣ «ሚያዚያ 10 ቀን 2007 ዓ.ም ቤታችንን ያቃጠሉት የአካባቢው ባለሥልጣናት «በየመሥሪያ ቤቱ ትዞራላችሁ የምታመጡት ነገር የለም፤ ዐርፋችሁ ካልተቀመጣችሁ ተጨማሪ እርምጃ እንወስዳለን» በማለት እያስፈራሯቸው እንደሆነ ተጎጂዎች በአካል ቀርበው ለሰመጉ አመልክተዋል::

ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የኢኮኖሚ የማኅበራዊና የባሕል መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 11(1) እያንዳንዱ ሰው በቂ ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ጨምሮ ለራሱና ለቤተሰቡ በቂ ኑሮ የማግኘት መብት እንዳለውና መንግሥት ደግሞ ይህን መብት የሚሟላት ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል:: የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 32(1) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በመረጠው የሐገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና መኖሪያ የመመሥረት ነጻነት አለው ሲል በግልጽ ይደነግጋል:: ዳሩ ግን ከዚህ ድንጋጌ ተቃራኒ በሆነ መልኩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል::

## 2. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

በአፋር ክልል ዞን 1 በአሳይታ ወረዳ በዋሙሌ ቀበሌ የተከሰተውን የቴምር ዛፍ መጨፍጨፍ እንዲጣራላቸው ለሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ጉዳቱ የደረሰባቸው አመልክተው ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ባለሙያዎችን ቦታው ድረስ በመላክና በማጣራት «በልማት ስም በዜጎች ላይ የሚፈጸም ማፈናቀልና የንብረት ማውደም በአስቸኳይ ይቁም!» በሚል ነሐሴ 26 ቀን 2007 ዓ.ም 138ኛ ልዩ መግለጫ ማውጣቱ ይታወሳል:: መግለጫውንም ለሚመለከታቸው የተለያዩ የመንግሥት አካላት እንዲደርሳቸው ቢያደርግም ምንም መፍትሔ እንዳላገኙ ጉዳቱ የደረሰባቸው አርሶ አደሮች ለሰመጉ በድጋሚ አመልክተዋል::

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 40 እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ንብረት የማፍራትና በንብረቱም በነጻነት የመጠቀም ሙሉ መብት እንዳለው እንዲሁም ለሚጠፋበት ንብረትና ማፈናቀል በቂና ተመጣጣኝ ካሣ የማግኘት መብት እንዳለው በግልጽ ደንግጓል:: በተጨማሪም ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የኢኮኖሚ የማኅበራዊና የባሕል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 11(1) እያንዳንዱ ሰው በቂ ምግብ ልብስ መጠለያን ጨምሮ ለራሱና ለቤተሰቡ በቂ ኑሮ የማግኘት መብት እንዳለውና መንግሥት ደግሞ ይህን መብት የማሟላት ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል::

## ማጠቃለያ

ዜጎች በሐገሪቱ የትኛውም አካባቢ ተዘዋውረው ኑሮ የመመሥረትና ሀብት የማፍራት መብት እንዳላቸው በሕገ-መንግሥቱ ተደንግጎ ሳለ በሌላ በኩል ደግሞ በቀበሌና በፖሊስ ባለሥልጣናት አባሎች መሪነት «የአካባቢው ተወላጆች አይደላችሁም» እየተባሉ በሕገ ወጥ መንገድ ቤቶቻቸው እየተቃጠሉባቸው ንብረቶቻቸውም እየወደሙባቸው ይገኛል። ይህም ድርጊት ከሐገሪቱ ሕጎችና ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች ጋር በእጅጉ እንደሚቃረን ሰመጉ ያምናል። ይህ ችግር በናኖ ወረዳና ኖኖ ቆንደላ ቀበሌ ብቻ የተከሰተ ሳይሆን በተለያዩ የሐገሪቱ ክልሎች ውስጥ በወረዳና በቀበሌ ባለሥልጣናት በሕግ አስፈጻሚና አስከባሪ አካላት የሚፈጸም መሆኑን ሰመጉ በተለያየ ጊዜ ካወጣቸው መግለጫዎች መመልከት ይቻላል።

የዚህ መብት ጥሰት ሰለባ የሆኑ ዜጎች ለረጅም ዓመታት ሠርተው ጥሪታቸውን በማፍሰስ የገነቧቸው መኖሪያ ቤቶች በማን አለብኝነት በእሳት እንዲቃጠሉ በመደረጉ አሁንም ያለምንም የመንግሥት ዕርዳታ በሜዳ ላይ ተበትነው ይገኛሉ። ዐቅመ ደካሞችና ሕፃናት እየታመሙ ያለበቂ ምግብና መጠለያ ጎዳና ላይ መውደቃቸው ሰብዓዊነትንና የሕግ መርሆዎችን የሚጻረር በመሆኑ ወንጀሉን የፈጸሙት የቀበሌና የወረዳ ፖሊስ አመራሮች ለፈጸሙት ወንጀል በሕግ ባለመጠየቃቸው በደል የደረሰባቸውን ተጎጂዎች ከማስፈራራት አልፈው ተጨማሪ ወንጀሎችን እየሠሩ ስለሚገኙ መንግሥት ወንጀል ፈጻሚዎችን ጊዜ ሳይሰጥ በአስቸኳይ ለሕግ እንዲያቀርብና ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች በቂ ትኩረት በመስጠት ችግራቸው መፍትሔ የሚያገኝበትን መንገድ ከሕዝቡ ጋር በመመካከር በአስቸኳይ እንዲፈልግ ሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል።

ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ዓለም ዓቀፍ መግለጫና የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተርን ጨምሮ በርካታ ዓለም ዓቀፍና አሕጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችን ተቀብላ የሕጎቿ አካል አድርጋለች። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 40(4፤7) የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት እንዲሁም ለደረሰባቸው የንብረት ጉዳት በቂ ካሣ የማግኘት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። በተጨማሪም የሰብዓዊ መብቶች ዓለም ዓቀፍ መግለጫ አንቀጽ 25 ማንኛውም ሕዝብ የተፈጥሮ ሀብቱንና ችሎታውን በሙሉና በነጻነት ለመጠቀም ያለውን መሠረታዊ መብት መንግሥት ማክበርና መጠበቅ እንዳለበት ይደነግጋል።

ይሁንና እነዚህ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች በመንግሥት ላይ የሚጥላቸውን ግዴታዎች ማለትም የመብት ማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታዎችን በመፈጸም ረገድ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል መሠረታዊ ችግሮች ይታያሉ። ስለዚህ በቂ ጥናትና ዝግጅት ተደርጎ በልማትና በግንባታ ስም ለተፈናቀሉና ንብረታቸውን ላጡ ዜጎች መንግሥት ተለዋጭ ቦታ እና ተመጣጣኝ የቋሳቋስና የሞራል ካሣ የሚከፍልበትን መንገድ እንዲያመቻች ከፊል አርብቶ አደሮችና አርሶ አደሮች የመሬት ዋስትናቸው ተረጋግጦ ያለሥጋት የሚሠሩበትና የሚኖሩበት ሁኔታ እንዲመቻች በተለይም ከሕግ ውጭ የቴምር ዛፋቸው ለወደመባቸው የአፋር ክልል አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ተገቢው ካሣ እንዲከፈል የቴምር ዛፎቹ እንዲጨፈጨፉ ባደረጉ አመራሮች ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድና ለወደፊቱም ለዜጎች የመሬት የንብረት ሠርቶ የመኖር ዋስትና እንዲሰጣቸው ሰመጉ አጥብቆ በድጋሚ ይጠይቃል።

**ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!!**



Human Rights Council